የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲፮
አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

19th Year No. 16
ADDIS ABABA 26th December 2012

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፭/፪ሺ፭ ዓ.ም

ለጌዶ - ለምለም በረሃ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአቡዳቢ የልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ..........ገጽ ፮ሺ፯፻፳

## CONTENTS

Proclamation No. 775/2012

Abu Dhabi Fund for Development Loan Agreement for Financing the Gedo – Lemlem Bereha Road Project Ratification Proclamation ....... Page 6720

### አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፭/፪ሺ፭

### በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአቡዳቢ የልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለጌዶ-ለምለም በረሃ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል መጠኑ ፴፮ ሚሊዮን ፯፻፴ሺ የኢምሬት ድርሃም (ሠላሳ ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሠላሳ ሺ የኢምሬት ድርሃም) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአቡዳቢ የልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ኦክቶበር ፱ ቀን ፪ሺ፲፪ በአቡዳቢ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታኅሣሥ ፱ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል::

### PROCLAMATION No. 775/2012.

### A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE ABU DHABI FUND FOR DEVELOPMENT

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Abu Dhabi Fund for Development stipulating that the Abu Dhabi Fund for Development provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan amount of 36,730,000 Emirates Dirhams (thirty six million seven hundred thirty thousand Emirates Dirhams) for financing the Gedo – Lemlem Bereha Road Project, was signed in Abu Dhabi on the 9th day of October, 2012;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 18th day of December, 2012;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

፩. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "ለጌዶ - ለምለም በረሃ የመንገድ ሥራ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከአቡዳቢ የልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፯፻፸፭/፪ሺ፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. **የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአቡዳቢ የልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ኦክቶበር ፱ ቀን ፪ሺ፲፪ በአቡዳቢ የተፈረመው የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

፫. **የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፴፮ ሚሊዮን ፯፻፴ሺ የኢምሬት ድርሃም (ሠላሳ ስድስት ሚሊዮን ሰባት መቶ ሠላሳ ሺ የኢምሬት ድርሃም) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

፬. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሳስ ፲፯ ቀን ፪ሺ፭ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **Short Title**

This Proclamation may be cited as the "Abu Dhabi Fund for Development Loan Agreement for Financing the Gedo – Lemlem Bereha Road Project Ratification Proclamation No. 775/2012".

2. **Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement signed between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Abu Dhabi Fund for Development in Abu Dhabi on the 9th day of October 2012, is hereby ratified.

3. **Power of the Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the loan amount of 36,730,000 Emirates Dirhams (thirty six million seven hundred thirty thousand Emirates Dirhams) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **Effective Date**

This Proclamation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 26th day of December, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ